# ስለ ኢትዮጵያ ሰላም

# በፓሪስ የተደረገው ኮንፈራንስ መግለጫ

ከመጋቢት ፩ እስከ መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ስለኢትዮጵያ ሰላም ለመነጋገር በፓሪስ የተደረገው ኮንፈረንስ የተዘጋጀው በፈረንሣይ ካቶሊኮች ፀረ - ረሀብና የልማት ኮሚቴ (CCFD) እና የሰው ልጅ እድገት ተራድኦ (FPH) ሲሆን በሥልጣን ላይ ያለው ኢህአዴግና ስምንት ዋና ዋና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ተጋብዘው ነበር። የኢህአዴግ አልሳተፍም ብሎ መቀረት ሁሉንም ቀር አሰኝቷል። የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአህድ) ከተጋበዙት ተቃዋሚ ኃይሎች አንዱ ሲሆን፣ የኢህአዴግ ባለሥልጣኖች ለልኡካኑ ካገር የመውጫ ይለፍ በመከልከላቸው ድርጅቱ በጉቤዔው ሊሣተፍ አልቻለም።

የተቀሩት በጉቤዔው የተሳተፉት ሰባት ድርጅቶች፣- የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራቲክ ህብረት (አአዴህ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) የኢትዮጵያ መድህን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድህን) የኢትዮጵያ ሕብረ - ብሔር ኮንግሬስ ፓርቲ (ኢህ-ብኮፓ) የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብ ረት(ዴኢህዴህ) የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) እና ትግራይ -ትግርኝ ኢትዮጵያ ናቸው።

እነዚህ ሰባት ድርጅቶች አገሪቱ የገጠማትን አሳሳቢ ሁኔታ በጥልቀትና በስፋት ከተወያዩ በኋላ በሙሉ ስምምነት የሚከተሉትን ግንዛቤዎች አድርገዋል።እንዲሁም በመቀጠል ላይ ያለውን ግጭት ለማስቆምና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነት ወዳለው የሽግግር ሥርዓት ለመድረስ የሚያስችል ሂደት (mechanism) ለመፍጠር ወስነዋል።

## ኮንፈረንሱ በሙሉ ስምምነት የሚከተሉትን ግንዛቤዎች አድርጓል።

## ፩ ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ

በሽግግሩ ሂደት ውስጥ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች በርካታ የሰብአዊ መብት መጣስ ተከስቷል። ግለሰ ቦች፣ ማህበራዊ ቡድኖችና ውሁዳን የህብረተሰብ ክፍሎች (minority communities) መብታቸው ተረግጧል። በሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች አባሎችና ደጋፊዎች ሌይ፣ በሽግግሩ ሥርዓት በተሣተፉትና በመሳተፍ ላይ ባሉት ጭምር፣ ህገወጥ የሆነ ክትትልና ማስጨነቅ ማስፈራራትና እሥራት ተፈጽሞባቸዋል።አዲስ አበባን በመንብኘት ላይ ለነበሩት የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አቤቱታ ለማቅረብ በሰላም መሰለፋቸው እንደወንጀል ተቆጥሮ፣ በቅርቡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተፈጸመው ግድያ ከተካሄዱት በርካታ ጭፍጨፋዎች አንዱ ነው።

አህአዴግ የቀድሞውን አገዛዝ መከላከያ ኃይል በማንአለብኝነት ለመበተን ባደረገው ውሳኔ ምክንያት በሺ የሚቆጠሩ ቤተሰቦቻቸው ለመናሪያ-አልባነትና ለለማኝነት መዳረጋቸው ኮንፈረንሱን ክፉኛ አሳዝኖታል።

## ፪ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን በተመለከተ

በኢህአዴግ በተወሰዱ በርካታ የፖለቲካ ውሳኔዎች፣ አቢይ የፖለቲካ ቡድኖች ከፖለቲካው ሂደት እንዲገለሉ መደረጋቸውን ጨመሮ፣ በመደራጀት ነፃነት ላይ የተጣለው ማእቀብና የተቃዋሚ ኃይሎች ህጋዊነት አግኝተው የመደራጀት፣ የመቀስቀስና የመሳተፍ መብት መነፈጋቸው ሂደቱን አጨናግፎታል።

## ፫ የሰኔ ወር ፲፱፻፹፬ ዓመት ምህረትን የክልል ምርጫ በተመለከተ

መራጮችን አለአግባብ ማስጨነቅ፣ ማስፈራራት እንዲሁም አንዳንድ የሽግግሩ መንግሥት አባል ዳርጅቶችን ጨምሮ፣ ከፍተኛ ተቃዋሚ ኃይሎች ከምርጫው መገለላቸው፣ ወይንም መውጣታቸው የሰኔ ፲፱፻፹፬ቱ የክልል ምርጫ አቢይ ጉድለቶች ናቸው። ስለሆነም ኮንፈረንሱ የሰኔውን የክልል ምርጫ ውጤት አይቀበለውም።

## ፬ ህግና ሥርዓትንና ብሄራዊ መከላከያን በተመለከተ

ወገናዊ የሆነው የአንድ ቡድን ወታደራዊ ክንፍ፣ እንዳለ ወደህገራዊ የፖሊስና የመከላከያ ኃይል መለወጡ፣ ኢህአዴግ በመንግሥታዊ ኃይል በመጠቀም የራሱን የፖለቲካ ዓላማ ለማራመድ አስችሎታል።

## ፭ የትጥቅ ግጭቶችን መስፋፋት በተመለከተ

ኢህአዴግ ተቃውሞን ለማፈንና ድርጅታዊ ፍላጎቱን ለመጫን ከዕለት ወደዕለት ወታደራዊ መፍተሄዎች መጠቀምን እያዘወተረ መጥቷል። በዚህ ሁኔታ የተነሳ በብዙ የሐገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ኢህአዴግ ከፍተኛ ወታደራዊ ዘመቻዎች በማካሄድ ነጹህን የሐገሪቱ ሰላማዊ ዜጎች ተጨፍጭፈዋል። መንደሮችም ተቃጥለዋል።

## ፮ የሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትና ወደፊት የሚደረገው የኤርትራ ሬፈረንደምን በተመለከተ

ኮንፈረንሱ በ1948 እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ውሳኔ መሠረት የሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ተፈጻሚነት አበክሮ ያረጋግጣል። በኢትዮጵያ በየጊዜው ሕዝባዊ መሠረት የሌላቸው መንግሥታት ተነስተው ከራሳቸው አልፎ ተከታዩን ትውልድ በልዩ ልዩ ግዴታዎች ውስጥ ሲያስገቡ ኖረዋል። አሁንም አገሪቱ ለህግ የማይገዛ፣ ከጠመንጃ ኃይል የሚያምን፣ ጠባብ ቡድን ሥር በመውደቋ፣ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ሕጋዊ ተፈጻሚነት እንደሌላቸው ከብዙ አቅጣጫ መግለጫ ተሰጥቶ አቋም ተወስዶበታል።

ይህ ሁኔታ እያለ የኤርትራ ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን ሬፈረንደም የማካሄድ ሁኔታ በመከሰቱና ይህንንም ህጋዊ ለማድረግ የኢትዩጵያ መንግሥት ድጋፍ ማስፈለጉ ሁኔታውን አወዛጋቢ አድርጎታል። በኢትዮጵያ የኢትዮጵያን ህዝቦች ግዴታ ውስጥ ማስገባት የሚችል ህጋዊ ውክልና ያለው መንግሥት ስለሌለ፣ ሁኔታዎች ተለውጠው፣ ሕዝባዊ መሠረት ያለው መንግሥት ሲቋቋም፣ የተለየ አቋም የመውሰድ መብቱ የተጠበቀ ነው። በኢትዮጵያ ባለው ባልተረጋጋ ሁኔታ ሬፈረንደሙ ፣ ሁሉንም ወገን ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ያሳተፈ ሊሆን መቻሉ አጠያያቂ ነው።

ስለዚህ የሚመለከታቸው ክፍሎች፣ የተባበሩት መንግሥታት ጭምር፣ በዚህ ጉዳይ ላይ "በሚወስዱት እርምጃ ይህ ህጋዊ ውዝግብ እንዳለ እንዲገነዘቡ እንጠይቃለን።

በሃምሌ ወር ፲፱፻፺፫ የተጀመረው የሽግግር ሂደት፣ በአመዛኙ ለዘላቂ ሰላም ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና ሀቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ለማስጀመር ያላስቻለ መሆኑን ግንዛቤ በማድረግ፣ በፓሪስ የተደረገው የኢትዮጵያ ሰላም ኮንፈረንስ የሚከትሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል።

፩ በተቻለ አጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉን-አቀፍ የሆነ፣ በኢተዮጵያ የሰላም እርቅ አገራዊ ኮንረንስ እንዲጠራ።

፪ የታቀደው የሰላም ዕርቅ ኮንፈረንስ ፍሬያማ እንዲሆን የኢህአዴግ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የፓሪሱ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ኢህአዴግ በመጪው ኮንፈረንስ ላይ እንዲሳተፍ አበክረው ይጠይቃሉ።

፫ የመጭውን ኮንፈረንስ ዝግጅት ተከታትሎ ለማስፈጸም ብሎም የኢትዮጵያ ህዝቦችና የአለም ሕብረተሰብን ድጋፍ ለማስገኘት የሰላምና የእርቅ ኮንፈረንስ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም፣

እንዲሁም ኮንፈረንሱ በአንድ ቃል የሚከተሉትን ጥሪዎች አስተላልፏል።

የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ባገር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች የኮንፈረንሱን ጥሪዎች እንዲደግፉ፣ ዘላቂ ሰላም ለማምጣትና እርቅን ለማውረድ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ፣
የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጆችና የዓለም ሕብረተስብ በሞላ በሔራዊ እርቅ ለማውረድ፣ ዘላቂ ሰላም ለማምጣትና ሃቀኛ ዴሞክራሲያዊነት ለማስፈን የምናደርገውን እርብርቦሽ እንዲደግፉ።

በመጨረሻው ፀረ-ረሀብና የልማት ኮሚቴ (CCFD) እና የሰው ልጅ እድገት ተራድኦ(FPH)፣ እንዲህም የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ የምርምር ማእከል (GRAPECA) አባሎችና አመራር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ላሳዩት ተቆርቋሪነትና ኮንፈረንሱ እውን እንዲሆን ላበረከቱት አስተዋጽኦ የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች በአንድ ድምጽ ከፍተኛ አድናቆታቸውንና ምሥጋናቸውን ይገልጣሉ።

በተጨማሪም፣ የፓሪሱን የኢትዮጵያ ሰላም ኮንፈረንስ በመደገፍ መልእክት ላስተላልፉት፣

፩ ለእውሮፓ ምክር ቤት ፕሬዚዳናታ

፪ ለአውሮፓ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት

፫ ለአውሮፓ ምክር ቤት ለሰው ልጅ መብት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት

፬ ለአውሮፖ ምክር ቤት ለልማትና ተራድኦ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት

፭ ለአውሮፓ ምክር ቤት ለአረንጓዴው ቡድን ጥምር ፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንሱ ያለውን አድናቆት ይገልፃል።

መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

ፓሪስ